# የአቧሬ ጉልት ገበያ ተቃጠለ፣ እሳቱን ለማጥፋት በሞከሩት ዜጎች ላይም የወያኔ ታጣቂዎች ተኩስ ከፍተው ቢያንስ ሁለት ሰዎች ሞቱ



ትናንት ታህሳስ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ (9.30 AM) ላይ አዲስ አበባ ውስጥ አቧሬ አካባቢ "ጉልት ገበያ" እየተባለ የሚጠራው ቦታ በእሳት መጋየቱ ታውቋል። በእሳቱ ምክንያት በርካታ ንብረት ወድሟል።





የእሳት አደጋ መኪኖች እሳቱን ለማጥፋት ጥረት አለማድረጋቸውና እንዲያውም እሳቱን ለማጥፋት የሚሞክሩትን ዜጎች የጸጥታ ኃይሎች ጥይት እየተኮሱ ሊያግዱ መሞክራቸው ወያኔ ሆን ብሎ ያቃጠለው ሳይሆን አይቀርም የሚል አስተያየት ብዙዎች እየሰጡ ነው። ቢያንስ ሁለት ሰዎች በጥይት ተመትተው መሞታቸው ታውቋል። ቦታውን ለከበርቴዎች ለመሸጥ የዜጎችን ንብረት ሙሉ በሙሉ ማውደም በጣም አሳዛኝ ድርጊት ከመሆኑ በላይ ይህ የጥፋት መልእክተኛ የሆነው ወያኔ በሕዝብ ኃይል ከስልጣን እስካልተወገደ ድረስ በሕዝብ ላይ የሚያደርሰው ግፍ ማለቂያ የሌለው መሆኑን ብዙዎች በቁጭት ተናግረዋል።